# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 45 ቁ 5** **ሐምሌ 2012**


## የት ደርሰናል?

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን፥ ሕዝቧም በእኩልነትና በአንድነት እንዲኖሩ፥ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ፣ በኢትዮጵያውያን ሙሉ ተሳትፎ በአገሪቱ ላይ የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥት በሕዝብ ውይይት እንዲጸድቅና ብሎም ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭነቱንና ባለቤትነቱን ተግባራዊ በማድረግ በራሱ ሙሉ ፈቃድ የሚያስተዳድረውን በሕግ አግባብ የሚመርጥበት፥ በመረጠው አካል ላይ እምነቱን ካጣ፣ የብቃት ጉድለት ካገኘ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ጥሠት ተፈፅሚል ባለበትም ወቅት መልሶ የመረጠውን ከሥልጣን የማውረድ መብቱ ይረጋገጥ ዘንድ ትግል ሲካሄድ ወደ ግማሽ ዓመት ተጠግቷል። ይሁን ይሁን እንጅ ሕዝባችን ለረጅም ዓመታት መስዋእትነትን እየከፈለ የጀመረውን ትግል ቢቀጥልም ዛሬም ከአምባገነን አገዛዝ ራሱን ማላቀቅ አልተቻለውም። መንግሥታዊ ሥልጣን ከባለነፍጥ ወደ ባለነፍጥ እየተዘዋወረ ቀጥሏል። ከዚህ አስከፊ አዙሪት ለመውጣት ባላባታዊውን ሥርዓት ታግሎ በማስወገድ በቦታው ሕዝብን ያማከለ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማቋቋም ይቻል ዘንድ ሕዝባዊ መንግሥት መመስረት ግድ እንደሚል ተገንዝቦ ትግሉን በማካሄድ ላይ አያለ ነበር ወታደራዊ ጁንታው ጣልቃ ገብቶ ልክ እንዳሁኑ አገዛዝ ሁሉ እኔ አውቅላችኋለሁ በሚል ሥልጣንን ከሕዝብ የነጠቀው። ከዚያም ያለ ምንም ደም በሚል እብሪትና ባዶ ጩኸት ለ 17 ዓመት አገሪቱን በልጆቿ ደም አቅልቶ፣ አንድ ተከላካይ ትውልድ ቅርጥፍ አርጎ በልቶ፣ ከውርደት በፊት ሞትን የሚሻ የትግል ወኔንና የዜግነት ክብርን ሰብሮ ወያኔ ለሚባል ዘረኛ አረመኔ አጋልጧት ፈረጠጠ። ይህንን ክፍተት የተመለከቱ ወትሮም ያልተኙላት ባዕዳን ኢትዮጵያዊነትን ከሞሶሎኒ ባልተናነሰ የሚጠላና የሚፈራ ዘረኛ ቡድን በብዙ ሚሊዮን ድጎማ አጠናክረው ለሥልጣን አበቁ። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ህልውናዋ ከፍተኛ አደጋ ላይ የወደቀው ከዚያ ከዚያ ከተረገመው ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. ጀምሮ ነው።

ኢሕአፓና በዙሪያው የተሰባሰበው ትውልድ ወደር በማይገኝለት የደም ታሪክ ህይወቱን የገበረለት የጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ትውልድ ተሻጋሪ በሆነ ትግል እየተካሄደ ቢቆይም በከሀዲ ምሁራንና ሉዓላዊነቷን በናቀውና በረገጠው የባዕድ አገር ሴራ የሕዝብን ዓላማ ከግብ ሳይደርስ መጨረሻው ሰዓት ላይ ድሉን ተነጠቀ። ይህ በጎጥ ዙሪያ የተሰባሰበና በፀረ-ኢትዮጵያነት የታነፀ ወሮበላ ቡድን በአሜሪካን አንቀልባ ታዝሎ አይበገሬ ልጆቿ ባለቁባት ኢትዮጵያ ላይ ሥልጣኑን አደላደለ። ወዲያውኑም ታሪካዊ የሆነችውን አገር ለመበተን ያሴረበትን ሰነድ ሕገ-መንግሥት ብሎ በሀገርና በሕዝብ ላይ ጫነ። በጊዜው ወያኔ ጠባብ ብሔረተኛና ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን በመሆኑ ሥልጣን በጁ ከገባ አገሪቱን በቀላሉ ወደማትወጣው ቀውስ ውስጥ እንደሚከታት የተገነዘበው ኢሕአፓ ሁሉን ያካተተ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም የትግል ጥሪ አድርጎና ተንቀሳቅሶ የአንድነት ድርጅቶች የተሰባሰቡበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃቅ) ሚያዚያ 1983 ዓ.ም. ተመሠረተ። ሆኖም በግንቦት 1983 ዓ.ም ፀረ ኢትዮጵያ በሆነው በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ የአፍሪካ ክፍል ምክትል ደኤታ ኸርማን ኮኸን ሰብሳቢነት ለንደን ላይ ሶስቱ ተገንጣይ ድርጅቶች (ወያኔ ኦነግና ሻዕቢያ ) ሥልጣኑ ያለቀለት ደርግ የውጪ

ጉዳይ ኃላፊ የነበረና ጥቂት ከሀዲ አዛውንቶች እንደሽማግሌ በተገኙበት፣ በወቅቱ ብዛት ያላቸው የአንድነት ድርጅቶችን ያካተተውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት(ኢዴኃቅ)ን፣ ኢሕአፓ ስላለበት ብቻ እንዳይገኝ መክረው አትዮጵያን አጥብቆ በሚጠላት በወያኔ እጅ እንድትወድቅ በየኑባት። በጊዜው ተነሳስቶ የነበረው የተቃውሞ እንቅስቃሴም ጊዜ እንስጣቸው በሚሉ አሸቃባጮችና የባዕዳን ተንኮል፣ ትውልድ ያለቀበት የትግል ውጤት ዳግም መነጠቁን በምፀት የምናስታውሰው የቅርብ ታሪካችን ነው ።

ወያኔም ደደቢት ላይ ያወጣውን መርሃ ግብር የአገዛዝ መርሆ አድርጎ በሥራ ላይ ለማዋል በስሩ በፈለፈላቸው በሙቶዎች የሚቆጠሩ የጎሳ ስብስቦች አማካኝነት፣ በማንነቱ ኮርቶ አንድ ሆኖ የኖረውን ሕዝብ በዘር ክልል አጠረው፤ ቀጥሎም አማራውን ጠላት አርጎ የጥላቻ መርዙን አሰራጨ። ብዙ ሳይቆይ በአርባ ጉጉ፣ በአሶሳ፣ በአደባባይ አየሱስ ወዘተ አማራው ላይ አጅግ አሰቃቂ ፍጅት አካሄደ፤ ትግራይ እንድትለማ ሌላው ሁሉ ይድማ በሚል ወታደራዊ ዘረኛ አንቅስቃሴ፣ አጎራባች የጎንደርና የወሎ መሬቶችን ነጠቀ። በተለይ በወልቃይት የኗሪዎቿን ማንነት አጥፍቶ ትግሬዎች በሚል ለመተካት ፍፁም አረመኔ የሆነ ዘር ማጥፋት ዘመቻ አካሄደ፤ ሀገሪቱንም ክልል በሚለው ፀያፍ ቃል በዘር አካለለ፤ ብሔራዊ ቋንቋን ወይም መሥሪያ ቋንቋን አዳክሞ የዜጎቿን ማኅበራዊና አገራዊ አንደነት ለማፍረስ ዘመቻ አካሄደ፤ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለመሻር ሕጋዊ መታወቂያው ላይ ሳይቀር የጎሳ ማንነት እንዲሰፍር አስገደደ፤ የችግርህ ሁሉ መንስኤ ነፍጠኛ አማራ ነው በሚል ቅስቀሳ ጠባብነትንና ዘረኝነትን አራገበ፤ ከፍፍሉን ለማጦዝ ሲል ምንም ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ባልተደረገበት የትምህርት አሰጣጥ በየቋንቋው ይሁን በሚል ትውልድ ገዳይ ፖሊሲ አፀደቀ፤ የብሔር ብሔረሰቦች መብት ብሎ ባወጣው አንቀፅም መገንጠልን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ነው ብሎ ሀገር አፍራሽ መርሆውን ይፋ አደረገ። ለአንድ ሀገር ብሔራዊ ደህንነትና ህልውና ቁልፍ ሥፍራ የሚሰጠውን የባህር በር እንዲዘጋ ለወዳጅ ቀርቶ ጠላትንም ባስገረመ ደረጃ ተሟግቶ አስፈፀመ። በመጨረሻም ኢትዮጵያን የሚያክል የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ቁጥር ያላት ሀገር ከውጭው ዓለም ጋር ለመገበያየት የሁለተኛ አገር ጥገኛ ሆነች። ሉአላዊነቷንና የግዛት አንድነቷን ለማስጠበቅ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አርበኞች የተሰውላትን አገር፣ ዳር ድንበሯን የፖለቲካ ጥቅሙ መሞዳሞጃ አደረገ። በ1990-92 ዓ.ም በሙቶ ሺዎች ያለቁበት የባድሜንም ጉዳይ እንዲሁ ደማቸውን ደመ ከልብ አደረገው፤ ወያኔ አገርን ከሥረ መሠርቱ ነቅሎ የዘረፈ ብቻ ሳይሆን ዘርፎ ለዘራፊ የሰጠ፣ ሀገርን ለመሬት ቅርምት አመቻችቶ ቁጥር ስፍር የሌለውን አርሶ አደር አርብቶ አደር አፈናቅሎ ሜዳ ላይ የበተነ ሀገርና ሕዝብ ላይ በታሪክ አቻ የማይገኝለት ወንጀል የፈፀመ ዘረኛ አገዛዝ ነው።

ይህ ዓይነት ፈታኝ የ27 ዓመታት ከፋፋይ ዘመቻና ፋሽስታዊ ሰቆቃ እየደረሰበት፣ ሕዝባችን ወያኔ ያጠመደው ቦምብ ሀገርን የሚያፈርስ እንደሆነ ተገንዝቦ በተቻለው አቅም ሁሉ ታግሎ ኢትዮጵያዊ ማነነቱን ጠብቆ በማቆየት አክሽፎታል። እንደሚታወሰው በ1997 ዓ.ም የሀገር ሀብት ዘረፎ የደለበውና የፖለቲካ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በራሱ ብሔር ተወላጆች መዳፍ መግባቱን የተማመነው የወያኔ ቡድን ምርጫ በሚለው ቧልት ውስጥ ዘና ብሎና ደፍሮ በከፈተው ውድድር ሕዝብ የማይረሳ ትምህርት ሰጥቶት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎሳ ወይም ሃይማኖት ሳይል በብሔራዊ መርሆዎች ዙሪያ ለተሰለፉ የአንድነት ኃይሎች (ለቅንጅትና ኅብረት) ድምፁን ሰጠ። ወያኔና ደጋፊዎቹ ባልጠበቁት የዜጎች ንቁነት ተደናገጡ። ወያኔ በጠራራ ሜዳ ሕዝብ አሸቀንጥሮ ሲጥለውና የለመደው ኮረጆ መገልበጥም አላዋጣው ሲል የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችንና ተመራጮችን ዘብጥያ አወረደ። ምርጫው መጭበርበሩን ተቃውመው የወጡ ወጣቶችንም በአልሞ ተኳሽ በሙቶዎቹ ገደለ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩትን በየማጎሪያ ጣቢያው አስሮ አሰቃየ፤ የብዙዎችንም መዳረሻቸውን አጠፋ። ከዚያም የአንድነት ኃይሉን ለማዳከም፣ የዘርና ሃይማኖት ከፍፍል ለማስፋት ያለ የሌለ ኃይሉን ሁሉ አሰማራ። በተለይም አሮሞውና አማራውን

የማለያየት ዓላማው ላይ ትኩረት ሰጥቶ በሰፊው ተንቀሳቀሰ ። ይህ አኩይ ተግባሩ ውጤት አላስገኘለትም የሚል ካለ፣ በስለላው መረብ ውስጥ ቱባ ባለሥልጣን የነበረውና በአድዋዎቹ ወንበር ላይ የተተካው ሹም ገና ቤተመንግሥቱን እግሩ እንደረገጠ ፀረ አማራና ፀረ ክርስትና የኦሮሞ ፅንፈኞችና የሚዲያ አሸባሪዎችን በክብር ጋብዞ በዙሪያው ማሰባሰቡን ልብ ይሏል። ዛሬ በአማራውና በክርስትና ሃይማኖት ላይ ፍጅት እያካሄደ ያለው ዘረኛ መንጋ አስከ መሪዎቹ የተፀነሰው ወያኔ ፌዴራሊዝም በሚለው የአፓርታይድ አገዛዝ መሆኑ መዘንጋት ያለበት አይመስለንም ። በመዲናዋም ላይ ኦሮሞ ልዩ ጥቅም አለው የሚለውን መሠሪ ስንኝም ሆነ፣ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ከናዝሬት ድንገት "ፊንፊኔ ኬኛ" መባሉም እንዲሁ። ሟቹ የወያኔ መሪም ሆነ አማካሪዎቹ መዘዙን ዘንግተውት አልነበረም። ወያኔም ሆነ ቡድኑን የተካው ዘረኛ አገዛዝ እጅግ ለሚጠሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት ምሳሌዎች ናቸው ብለው ጥርስ በነከሱባቸው የኢትዮጵያ ከተሞች ላይ መንጋ እያደራጁ ለዕልቂት ከማሰማራታቸው በፊት እርሻውን ያዘጋጁት ቀደም ብለው ነበር። ድሬዳዋን በ40/40/20 የዘር ግንድ የሸነሸኑትን ልብ ይሏል። እዚህ ላይ ነገሮች የተለወጡ በመሰሉ ቁጥር እንዴት ራሳቸውን በአዲስ መልክ እንደደገሙ ለመጠቆም ያህል እንጂ ወያኔ ኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን በደል ወይም የፈፀመውን ወንጀል እንዲህ በቀላሉ ዘርዝሮ መጨረስ ይከብዳል።

ይህ የወያኔ ግፍ ሞልቶ ከፈሰሰ ውሎ አድሯልና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ትዕግስት ያለቦታው ሀገር እንደሚያሳጣ አስተውሎ ታግሎታል። በ27 የመከራ ዓመታት ውስጥ ብዙ የሕይወት ዋጋም ከፍሏል። ትግሉ አንዴ እየተፋፋመ ሌላ ጊዜ እየተደናቀፈም ቢሆን አልቆመም። የትግል ጉልበቱ ቀጣይነቱ ነውና ሞት፣ እስራት፣ እንግልት ለሀገርና ለወገን ስርየት የሚከፈል ዋጋ መሆኑን ተገንዝቦ ሕዝብ ቆርጦ ከተነሳ፣ የትኛውንም አይነት አብሪት ያሳበጠውን አምባገነን ከተራራ ጫፍ ላይ አውርዶ እንደሚጥለው ታሪክ ምስክር ነው። ወያኔም ከዚሁ ታሪካዊ እውነታ አላመለጠም። ማኅበራዊ ፍትህን ለማስፈን ታላቅ ራዕይ አንግቦ ለሚነሳ ሁሉ የሚከብደውን ያህል፣ ማንብደድና ራስ ወዳድነት ስር እንዲሰድ ከተፈቀደለት በጥቂት ግብዞች እጅ መፍረሱም በተቃራኒው የቀለለ ሊሆን ይችላል።

የ27 ዓመት የወያኔ ቡድን ዘረኛ አገዛዝ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንግዲህስ በቃን! እስራትና ሞት ከትግል አይገታንም ብሎ ቆርጦ ተነሳ። በመሆኑም ቀስ በቀስ ትግሉ እየተፋፋመ ሄዶ፣ በ2010 ዓ.ም አገዛዙ በለመደው መንገድ መግዛት ያልቻለበትና ሕዝብም ከእንግዲህ አልገዛም ብሎ ማንቁርቱን የያዘበት ወሳኝ ደረጃ ላይ ደረሰ። ከዚህ በተጨማሪ አገዛዙ በውስጥ ቅራኔና ሙስና መንቀዙ ውድቀቱን አቀረበው። ኦሮሞና አማራውን አለያይቸ ገና መቶ ዓመት አገዛለሁ በሚል ትዕቢት የተወጠረውን የወያኔ ፊኛ "የኦሮሞው ደም ደማችን ነው" "የአማራው ደም ደማችን ነው" በማለት በአንድነት ተነስቶ አስተነፈሰለት። የአምስት ለአንዱን የቁጥጥር ሰንሰለትም በጣጥሶ ጣለለት። ይህ ብቻ ሳይሆን በገፍ ለማሰርና ለመግደል በአጠቃላይ ትግሉን ለማፈን ያስችለኛል በሚል በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ተከታታይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቢያውጅም፣ በየአቅጣጫው የተቀጣጠለው የሕዝብ ትግል አንደቋያ እሳት ሲለበልበውና ሕዝብ ሞትን ንቆ እንደተነሳበት ሲረዳ፣ በጣረ ሞቱ ላይ የደረሰው ዘረኛ አገዛዝ "አዎ በስብሰናል ጥልቅ ተሀድሶ ያስፈልገናል" በማለት ሕዝብን ሊደልል ሞከረ።

ሕዝብ ትግላችንን ከግብ ሳናደርስ ወይ ፍንክች ብሎ ወያኔን ከነግሳንግሱ ጠራርጎ አስወግዶ ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር የሚጀመርበትና ታሪካዊ የሥልጣን ምንጭነቱን የሚረጋገጥበት አዲስ ተስፋና የአዲስ ሥርዓት አጥቢያ ላይ ደርሶ ነበር። በዚህ ተስፋ ሰጭ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር በባዕዳን ሴራ የወያኔው ምልምል ኮሎኔል የለውጥ ኃይል ነው በሚል ጫጫታና ማሻሻጫ በላዩ ላይ የተሰየመበት። ልዕለ ኃያልነቱን የያዘው አሜሪካም እያደር ማን አለብኝነትን እንጅ በኢትዮጵያ ላይ የውጭ ፖሊሲውን መልሶ ለመመርመር ፈቃደኛ አልሆነም። እንዲያውም ይበልጥ በአገሪቱ ህልውና ላይ የተነሱ

ፅንፈኞችንና ከሀዲ ምሁራንን በመጠቀም በሚያስገርም ትርክትና ትወና የአገዛዙን ካድሬዎችና የደህንነት ባለሟሎች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አልብሰውና የሕዝብን ድምፅ በማስጮህ፣ ብዙዎች ውድ ህይወታቸውን የከፈሉበትን፣ የተጋዙበትንና የተሰቃዩበትን የትግል ውጤት ቀምተው የሃገሪቱንና የሕዝቧን ሉአላዊ መብት ዳግም ረገጡ። አገሪቱንም ልክ ወያኔ በትግራይ ስም ይነግድ እንደነበረው፣ ሀገሩን ወዳድና ወገኑን አክባሪ የሆነውን የኦሮሞ ሕዝብ የዘር ጥላቻ ማራገቢያ፣ የአምባገነን አገዛዙን ዕድሜ ማራዘሚያ አድርጎ የሚጠቀም ብልጥ ባይ ኮሎኔል እጅ አስገቧት። በ1983 የኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም የወገን ኃይል በሌለበት የወያኔን ጎጠኛ ቡድን የሾሙበትን የማናለብኝ ድርጊት በ2010 ደገሙት። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ነውና ዜጎች ሀገራቸውን ነቅተው ካልተከላከሉና የመጣውን አፈጮሌ ሁሉ ሙሴ ነው ብለው ከሰገዱ፣ ኃያሉ ቀርቶ ድኻው ጎረቤት ሀገርም ድንበራችንን ጥሶ ገብቶ ወታደሩን መሬታችን ላይ ማስፈሩ እኮ የታየ ሐቅ ከሆነ ሰንብቷል።

በድጋሚ አጽንኦት ሰጥቶ መገንዘብ የሚያስፈልገው ሀገር መገንባት ታላቅ ራዕይ ይዞ ለሚነሳ የሚከብደውን ያህል፣ በአንፃሩ ማጎብደድና ራስ ወዳድነት ስር ከሰደደ በጥቂት ህሊናቢሶች በቀላሉ ሊፈርስ ይችላል። ትናንት የወያኔ መሳሪያዎች የነበሩ ናቸው ዛሬ መሳቂያ በሆነ ተረት ተረት መንጋ አሰማርተው ዜጎቿን እያሳረዱ የባዕዳንን መሠሪ ተልዕኮ እየተወጡ ያሉት። አለመታደል ሆነ አንጂ፣ በዚህ ጊዜ ነበር ወገን በተራብ አንጀቱ ግብር ከፍሎ ያስተማራቸው ምሁራን፣ በለስ ቀንቶት ቤተመንግሥት የገባውን ሁሉ ከማወደስ ይልቅ፣ ሕዝብን እኔ አውቅልሃለሁ ለሚል አምባገነን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተከብሮ፤ በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ አገራዊና ሕዝባዊ አንድነቱ ተጠብቆ፣ ከማያባራ ሰቆቃ እፎይታ አግኝቶ፣ አገሩንና የራሱን የኑሮ ደረጃ የሚያሳድግበት እድል ባለቤት ለመሆን እንዲበቃ የትግሉ ፋና ወጊ መሆን ይጠበቅባቸው ነበር። የተወሳሰበውን አፍታቶና የተጣመመውን አቃንቶ ሕዝብ የራሱ ዕድል ባለቤት ማድረግ ኃላፊነታቸው ነበር። በአገራችን ዛሬ ላይ  የሆነው ግን ፍፁም ተቃራኒ ነው። ሕዝብ ታግሎ ካወረደው ዘረኛ አገዛዝ አብራክ የወጣውን አፈ ጮሌ እንዲሰየምበት ያለምንም ሀፍረት ተባበሩ። በነዚሁ ከፍሎች የክህደት ጭብጨባ ታጅቦ የትናንቱ የወያኔ ሰላይ ኮሎኔል በብርሃን ፍጥነት ቀለሙን ቀይሮ ቦታው ላይ ተቀመጠ። ይህ የጎጥ ከፍፍልን ለማጦዝ ቀደም ሲል አወሊያን ያቆመ ፀረ ኢትዮጵያ እና ፀረ አማራ የትሮይ ፈረስ፣ ድብቅ ተልዕኮውን ለመወጣት ባገኘው ዕድል ተሳክሮ በዘር ጥላቻ የደነደኑ ኦነጎችን ከነትጥቃቸው ማስገባቱ አንሶት፣ ጎራዴያችን በክርስቲያንና የአማራ ደም ይቀላል ባዩን ባለሜንጫ ከሚዲያ መድረኩ፣ በተቃዋሚ ሽፋን ከሻዕቢያ ጋር ገጥመው አርበኞችን ያሳፈኑና በውጭ ያለውን ማኅበረሰብ በሀሰት ወሬ ገንዘቡን የዘረፉ፣ የአንድነቱን ኃይል ለማዳከም ኦነግን ከመቃብሩ ያውጡ ቅጥረኞችን፣ ከሀዲ አንጃዎችንና አጠቃላይ ፀረ ሕዝብ ግለሰቦችን በክብር ጠርቶ በዙሪያው አሰለፈ።

ወትሮውንስ ሹሙ በፀረ ሕዝብነቱ ሰይጣንን የሚያስንቅ ባይሆን ኑሮ የአድዋዎቹን ቀለበት አልፎ የደህንነቱ ቁልፍ ቦታ ላይ ባላስቀመጠው ነበር። አይነቁም በሚል ይመስላል ሰላሳ ጊዜ የኢትዮጵያን ስም ጠርቶ ዲስኩር ቢያበዛም፣ ላይላዩን እያባበልክ ውስጥ ውስጡን አፅዳ ስልት አርጎ እንድሚጠቀም ገና ከጠዋቱ የነቁበት ቢኖሩም፣ በመንጋ የሚነዳውን ቀልብ እስካሁን ስቦለታል። ይኸው ሰሞኑን አጨብጭበው ለቤተመንግስት ያበቁትና ተመክሮ ከስሜት ጉዞ ያላገዳቸው የዕድሜ አዛውንቶች፣ ኮሎኔሉ ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ አስካሁን ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን በደል አናይም ብለው ድጋፍ ሲያሰባስቡለት እየታዘብን ነው። ለሚያስተውል ዜጋ ስውር ያልሆነው ጉዳይ፣ ኦፒዲኦ በሚል ወያኔ የፈጠረው የኦሮሞ ክንፍ፣ ኦነግ በተወሰኑ ዓመታት አማራና ክርስቲያኑን ከኦሮሚያ ለማፅዳት (የዘር አልፂት ማካሄድ ማለት ነው) በዕቅድ ያቆየውን ዓላማ እያስፈፀመ ለመሆኑ በመከላከያ፣ በፀጥታ፣ በአስተዳደር ቁልፍ በሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማትና ብልፅግና በሚለው ጉረኖ ውስጥ የተሰገሰጉትን የኦሮሞ ፅንፈኞች ማየቱ ብቻ በቂ ነው።

ኮሎኔሉ አገዛዙን በያዘባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ በሀገርና በሕዝብ ላይ የደረሰውን ፍጅት፣ መከራና ግፍ ለተመለከተ ወያኔዎች እንዴት 27 ዓመት ወሰደባቸው ሳያሰኘው አይቀርም። አገዛዙን በያዘ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 3 ሚሊዮን ዜጎቿን በማፈናቀል በዓለም የመጀመሪያ ቦታ እንድትይዝ አድርጓታል። እየደረሰ ላለው ዘርና ሃይማኖት ተኮር ጭፍጨፋ መንስኤ የሆነው ወያኔ  በሀገር ላይ የጫነውን ሕገ አራዊት፣ ሕገ መንግሥቱን ላስከብር ነው የመጣሁት ማለቱ አነሰ ብሎ፣ ሰሞኑን አገሪቱን እያመሱ ባሉ ፅንፈኞች ሴራ ተገደለ የተባለውን የኦሮሞ ዘፋኝ ሀጫሉ ሁንዴሳን ህልፈት ተከትሎ ባለሜንጫውን መንጋ በኢሱዙ እያጓጓዙ በየከተማው አሰማርተው ዜጎችን በብሔራቸውና ሃይማኖታቸው ምክንያት የስም ዝርዝር ይዘው ቤት ለቤት እየሄዱ፣ ህጻናት፣ አዛውንት፣ እርጉዝ ሴት ሳይሉ አረዱ፣ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ አረመኔነት ቀጥቅጠውና ከታትፈው ገደሉ፣ በመላ ቤተሰብ ላይ በር ዘግተው በሳት አነደዱ፣ የሰለባቸውን ሬሳ ልኳንዳ ቤት ዘቅዝቀው ሰቀሉ፣ መንገድ ለመንገድ ጎተቱ፣ በሻሸመኔ፣ አሩሲ ነጌሌ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረር፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ፣ አጣየ፣ አሳሳ፣ ጌዴዎ ወዘ... በተካሄደ የዘር ማጥፋት ሰለባ የሆነውን  ሕይወትና ንብረት ቤት ይቁጠረው። ይህ ሁሉ ሕይወትና ንብረት ሲጠፋ በሻሸመኔ ከ800 በላይ የኦሮሚያ ፖሊሶችና የደቡብ ዕዝ አንድ ብርጌድ፣ ከሻሸመኔ ሰባት ኪ/ሜ ርቀት የደቡብ ዕዝ ማዘዣና በ 27 ኪ/ሜ ርቀት ወንዶ ጢቃ ላይ አንድ ብርጌድ የአየር ሃይል ባለበት አገር ነው መንጋው ሕይውት እንዲቀስፍ ንብረት አንዲያወድም የተለቀቀው ። ዘረኛው ኮሎኔል መከላከያ ኃይሉን የሚጠቀመው አማራውን ለማጥቃት ሲፈልግ ብቻ መሆኑ ግልፅ ነው። አገዛዙ አማራውን ሲያጠቃና ሲያስጠቃ 28 የመከራ ዓመታት እንዳሳለፈ የተረዳው ጀኔራል፥ አማራው ከሚደርስበት ጥቃት ራሱን ይከላከል ዘንድ ለልዩ ኃይል የተወሰኑትን ለማሰልጠን በመሞከሩ፣ ኩዴታ ተካሄደ በሚል ሰበብ ኮሎኔሉ ጦሩን ባህርዳር ያስገባው በደቂቃዎች ውስጥ ነበር። በአንፃሩ ግን በኦሮሚያ በቁጥሩ ሽህ ጊዜ እጥፍ የሚሆነው 31 ዙር ልዩ ኃይል ሰልጥኖ ሲመረቅ በተወሰነ የምረቃ ስነሥርዓትም የተገኘው ኮሎኔል ጭራሽ በፀረ አማራነቱ የተኩራራ ነው የሚመስለው። ከዚህ ጋር የተያያዘ ሌላው የአገዛዙ አሳዛኝና ቅጥ ያጣ ዘረኝነትን የሚያመላክተው፣ ባለፈው ዓመትም ሆነ ሰሞኑን ከደረሰው የዘር ፍጅት እንደታየው፥ መከላከያው በቦታው የሚደርሰው ከበረደና ሰው ካለቀ በኋላ መሆኑ ነው ።

ይህ ሁሉ ወንጀል በሕዝብ እና በሀገር ላይ ሲደርስ ለምን ሕግ አታስከብርም ተብሎ ሲጠየቅ፣ “እኔ የሰፈር ሚሊሽያ አይደለሁም” በሚልም ተሳልቋል። ይህም ከወንጀለኞች ተርታ የሚያሰልፈው ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ለሕዝብ ንቀት እንዳለው የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል በወያኔ ተኮትኩቶ ያደገና ከቀድሞ አለቆቹ ጋርም ቢኮራረፍ መሠረታዊ መርሆዎች ላይ አንድ መሆኑ እየታወቀ ከዚህ የተለየ ምን እንዲሆን ጠብቃችሁ ነበር ለሚሉ፣ ጥያቄው ለኛ ሳይሆን ትናንት የኖቤል ሽልማት ይሰጠው፣ የዘመናችን ሙሴ ምንትስዬ ሲሉ ለነበሩና ዛሬም ፅንፈኞችን አሰረ በሚል በተለመደው ጭብጨባ የነጎዱትን ይመለከታል። ለመሆኑ ሲጀመርስ ጽንፈኞቹን፣ ባለሜንጫ አሸባሪዎችን፣ የዘርና ሃይማኖት ማሰራጫ ጣቢያወች ሳይቀሩ ማነው ከያሉበትና ከተበታተኑበት ግቡ ብሎ ያሰባሰባቸው? ማንስ ነው የድኻይቱን አገር አንጡራ ሀብት በሚሊዮኖቹ እያፈሰሰ ሀገር ውስጥ ኑሯቸውንና ደህንነታቸውን የተንከባከበው? የዘር ማጥፋት ዓላማቸውን ለማሳካት ባለሜንጫ መንጋዎችን ሲያደራጁ፣ ይህ አሁን የምናየውን እንደሚያስከትል ለቀድሞው የደህንነት ሹም ሚስጥር ሆኖበት አይደለም። እነዚህ አረመኔዎች የሰው ፍጡር መሆናቸውን አከራካሪ በሚያደርግ አረመኔነት በግፍ ሲያርዱ አለማስቆሙ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ራሳቸውን ሊከላከሉ የሞከሩትን የሚያጠቃው ጦር ሥልጣኑ ከፌዴራል ተብየው በላይ ነው እያለን ነው? ባለፈው ዓመት በዘርና ሃይማኖታቸው ምክንያት ትናንት በግፍ የተጨፈጨፉትን፣ አብዛኛው አሮሞዎች ናቸው ብሎ ሀፍረተቢስ ዘረኝነቱን ይፋ ያደረገውን ኮሎኔል፣ ጎራዴያችን በክርስቲያንና የአማራ ደም ይቀላል ሲል የባጀውን የአረብ ተላላኪ ወደ ሀገር ያስገባውና የገንዘብ ድጎማ ያደረገለትስ ማን ሆነና ነው? ዛሬ ጽንፈኞችን አስሯልና ቆብ ይውልቅለ የሚባለው? በዚህ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ  በዚሁ ግለሰብ ጥሪ ከ 97 በላይ ንጹሃን ሲገደሉ መች በግለሰቡ ላይ እርምጃ

ተወሰደ? ዛሬ ኮሎኔሉ ጋዜጠኞችን ለመያዝ የተገደደው በሥልጣኑ ስለመጡበት እንጅ ተይዘው ለፍርድ መቅረብ የነበረባቸው ይህ ሁሉ ፍጅት ሳይደርስ ነበር። ያ ወደ ሀረሬ የፈረጠጠው ሰው በላ "አብዮት ልጇን ትበላለች" ብሎ ወዳጆቹን አልበላም እንዴ? የዛሬው ኮሎኔል ሥልጣኔ ላይ መጡብኝ ብሎ ጥቂት ጓዶቹን ማሰሩን ተከትሎ የሚታየው የአብይን ደግፉ ጭብጨባ፣ ጦሩን አስረህ ይዘህ ሕዝቡን አታስጨርስ፣  የሽግግር ሂደት አሁኑኑ ይጀመር፣ በሚል በተተካ ነበር። ደሞዙን ከፋዩ ሕዝብ በሰው በላ መንጋ ሲታረድ መከላከያውን እንደ ግል ንብረቱ ጠፍሮ ይዞ ግዴታውን እንዳይወጣ በማድረጉ በግፍ ላለቁት ተጠያቂ ለመሆኑ የሕግ ባለሞያ መሆንን አይጠይቅም። ኮሎኔሉ በዚህ ኮቪድ መንቀሳቀሻ ባሳጣበት አስከፊ ወቅት ጦሩን፣ ታንክ ሳይቀር አንጋግቶ የጎንደር ሕዝብ ላይ ማንቀሳቀሱ ይታወሳል። ጦሩን መምዘዝ የሚቀናው አማራው ላይ ብቻ መሆኑ ነው። በኦሮሞ አሸባሪዎች ከደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ የታገቱትና ብዙዎቹ ልጃገረዶቹ የሆኑት 17 የአማራ ወጣቶች መዳረሻቸው ከጠፋ እነሆ ከስምንት ወር በላይ ሆናቸው። ኮሎኔሉ ጭራሽ መሠረት የሌለው የተምታታ መግለጫ በመስጠት አድበስብሶታል። ይባስ ብሎ የት ደረሱ ብለው የሚጠይቁትን ቤተሰቦች ሳይቀር በማሸማቀቅ አፋቸውን ሊያዘጋ ነው የሞከረው። ከሰሞኑ ደግሞ የት ደረሱ ለሚለው መልስ ሳይኖረው ከታጋቾቹ ጋር በተያያዘ ተጠርጣሪዎችን አስረናል ብሏል። አገዛዙ አስካሁን ባሳየው ባህሪ፣ ሀገሪቱ በወሮበላዎች፣ በኦነግ አሸባሪዎች፣ በሾማቸው ፅንፈኞች አነሳሽነት በቄሮ መንጋ ፍጅትና የንብረት ውድመት አገሪቱ እንድትታወክ ምንም ባለማድረግ በተግባር ትብብሩን አሳይቷል።

ሌባ ከፍፍል ላይ እንደሚጣላው ዘረኞቹም በወንበር ሽሚያ ግብግብ ቢገጥሙ አያስገርምም። ኢትዮጵያን በማፍረስ ዓላማ የተቆራኙት ጠላቶቿ ሲስማሙ ነው መጨነቅ እንጅ ሲጣሉማ እሰየው ብሎ ይልቅስ ቅራኔያቸውን ይበልጥ በማባባስ አደገኛ ቀውስ ውስጥ የከተቷትን አገር ለማዳን መጠቀም ከብልህ ዜጎች የሚጠበቅ ነበር። እዚህ ላይ የምንለይበትን ግልፅ ለማድረግ፣ ኮሎኔሉ ያሰራቸው የኦሮሞ ፅንፈኞች አማራውና ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ ላይ ፍጅት ማካሄዳቸው ወይም የሀገር ህልውና ላይ የተቃጣው አደጋ አሳስቦት ሳይሆን፣ ከላይ እንዳልነው በሥልጣኑ ላይ ስለመጡበት ብቻ ነው ። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ የባልደራሱ መሪ በመዲናዋ ኗሪዎች ላይ የሚካሄደውን የአንድ ብሔር ባለቤትነትን፣ የመሬት መቀራመትን፣ በውድቅት ሌሊት ቤታቸው በባለጊዜዎች እየፈረሰ ሜዳ ላይ የሚበተኑ ዜጎችን ጉዳይ በማገለጡ እና የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ ይከበር በማለቱ የሚያሳስረው ሆኖ አይደለም። ሌሎችንም እንዲሁ የኦሮሞው ፅንፍ ያልሆኑ የድርጅት መሪ ነን የሚሉ ግለሰቦች ምናልባት ከመቀሌ የሥልጣን ተቀናቃኞቹ ጋር በተያያዘ ሆነም አልሆነም አስሯል። ሌሎችም ብዙ ስማቸው ያልታወቀ እንዲሁ መታሰራቸው ሚስጥር አይደለም። ዋና ዓላማው እሱ ከሚያዘው ፓርቲ ያልተጠቃለሉትን አፋቸውን አዘግቶ ብልፅግና እያለ በሚጠራው የአህዴድ ጥርቅም አማካኝነት ፍፁም አምባገነን ሆኖ የሚወጣበትን መንገድ ለማመቻቸት ነው። የሰሜኑ ጫፍ ጥብቅ ወዳጁም በእንዲህ ዓይነቱ ሽፍጥ የተካነ በመሆኑ ትልቅ አርአያ እንደሚሆነው መገመት አያዳግትም። ቀደብ ብሎ ኢሳያስ የፈጠራቸው የአድዋ ጡት ልጆቹ በለስ ወንበር ይዘው ወፈር ሲሉ ዞር በል ብለው ከኢትዮጵያ ካስወጡት ከሃያ ዓመት በኋላ፣ ልክ እንደሚቹ የወያኔ መሪ በአድናቆት የሚሽቆጠቆጥለት በማግኘቱ እሱም በለስ ቀንቶታል ማለት ይቻላል። በአንድ በኩል ከኢትዮጵያ ያገኝ የነበረውን ጥቅም መልሶ ማስጠበቅ እድሉ በመስፋቱ፣ በሌላ በኩል እሱን በማስወገድ የትግራይ ትግሪኝ ህልሙን ዕውን ለማድረግ ሲንደፋደፍ የቆየውን የመቀሌ በረሮ ቢያንስ ክንፉን መስበር ይቻላል የሚል እምነት በመያዙ  ፍላጎቱን ሁለቱን ከተሞች ላይ ቤትና ታች ቤት ካደረገው ኮሎኔል ጋር አይመክርም ማለት አይቻልም።

ኢትዮጵያ ዛሬ በአራቱም ማዕዘን በብሔር ጽንፈኞች በተቀሰቀሰ ቀውስ እየታወከች ያለችበትና ህልውናዋም ከፍተኛ አደጋ ላይ የወደቀበት ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ዜጎቿም በብሔራቸውና ሃይማኖታቸው ምክንያት ያለተከላካይ እየተፈጁ ነው።

በማንነታቸው በሚያፍሩ፣ በብሔር ጥያቄ ሽፋን በበታችነት ስሜት ታውከው ሲያውኳት የቆዩ ዘረኞች በባዕዳን ሠፌ ድጋፍ ታጥቀውና ጉልበት አግኝተው ዜጎቿንም፣ በሙቶ በሚቆጠሩ የዘር ፓርቲዎች በማራባት፣ በመከፋፈልና በማዋከብ አቅም አሳጥተው በትረ መንግሥቱን በነፍጥ ከያዙ ሰላሳ ዓመት በኋላ አገራችንን እዚህ ደረጃ ላይ ሊያደርሷት በቅተዋል። አሁን መቀሌ ላይ የመሸገው አውሬ የዘረጋው ዘረኛ አስተዳደር በተረኛ ኮሎኔል ትኩስ ጉልበት አግኝቶ የገሀነምን በር በወገኖቻችን ላይ ከፍቶባቸዋል። የወያኔ ግርፍ ነውና መሠሪነትን ይበልጥ ተከኖበት ብዙ የሀገሪቱን ዜጎች በቃላት እያጃጃለ አባቶቻቸውና አያቶቻቸው በደምና በአጥንታቸው ዋጋ ከፍለው ባቆዩአት አገር ልጆቿን የባርነት ቀንበር ሊጭንባቸው ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል። ሀገሪቱም በሹም የምትገዛ በመሆኗ ሉአዊነቷን ካጣች እንዲሁ ቆይታለች። ኦሮሞውን ከአማራው ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑን ከሙስሊሙ ደም ለማፋሰስ 30 ዓመት ባዘኑ፣ ሆኖም ብዙኀኑ ኢትዮጵያውያን ለረጅም ዘመናት የተሳሰረና የተጋመደ አትዮጵያዊ ማንነትና የጋራ ታሪክ ያላቸው በመሆኑ በሥልጣን ላይ ያሉ ቡድኖችና ጽንፈኞች በዘረጉት ወጥመድ ወስጥ አልገቡም። ዘረኞች እቅዳቸውን ሲያከሽፍባቸው መጥረቢያና ቆንጨራ የታጠቀ በዘር ጥላቻ የወጠሩትን የቄሮ መንጋ በትራክ አያጓጓዙ አዘመቱ። መታውቅ ያለበት ዋና ጉዳይ፣ የኦሮሞ ጎረቤት በሌላ ብሔር ጎረቤቱ ላይ አልተነሳም፤ እንዲያውም ብዙዎችን ደብቆ ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሞከረ እንጂ። በጥላቻ ስብከት አነሁልለው ሕዝብን የሚያሳርዱት አገዛዙ በተለያየ የሥልጣን እርከን ያስቀመጣቸው ዘረኞች ናቸው። ከአማራና ከክርስቲያን የፀዳች ኦሮሚያን ገንጥለን የራሳችን መንግሥት እንመሥርታልን የሚሉ፣ በአንድ በኩል፣ ኢትዮጵያን በገዳ ሥርዓት ወይም በኦሮሞው የበላይነት መግዛት ይቻላል የሚሉ በሌላ በኩል የበላይነትን ለመያዝ መጠላለፍ ቢኖርም፣ ሁሉም አማራውንና ክርስቲያኑን የሚያጠቁ ናቸው። በሌላ በኩል የተፈጠረውን ቀውስ በማስፋት ወያኔ ሥልጣን የማስመለስ ቅዥቱን እውን ለማድረግ በቀውሱ ውስጥ የሚታየው አሻራው ብቻ ሳይሆን መዋቅሩም መኖሩ ሚስጥር አይደለም። በአገዛዙና በወያኔ መሀል የተፈጠረው ልዩነት እየከረረ መምጣቱን ከሚያስተላልፉት የቃላት ጦርነት አልፎ መቀሌ የመሸገው አውሬ ፣ አገዛዙ ጥቃት ሊሰነዝርብን ነው በሚል ወጣቱን ለወታደራዊ ግዳጅ ጠርቷል። ኮሎኔሉ መጀመሪያስ ቢሆን መቀሌ ሄዶ እነ መለስን ከማወደስ ይልቅ ይህን ራሱን እንደ ገለልተኛ ሀገር አስቀምጦ፤ በሕግ ሳይገዛ በጀት የሚሻማውን ቡድን መስመር ባስያዝ ነበር። በዚህም ተባለ በዚያ፣ ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው፣ እነዚህ ፀረ አትዮጵያ ኃይላት ዝም ተብለው ከተለቀቁ የሚያስከትሉት ጉዳት እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። የውጭ ኃይሎችም እኩይ ተግባር እንደዚሁ ለቀውሱ መባባስ ነዳጅ እየሆነ መጥቷል።

እናም የት ደርሰናል ለሚለው ጥያቄያችን መልሱ በኛ በኩል ፍንትው ብሎ የሚታይ መሆኑን ከዚህ በላይ ለማሳየት ሞክረናል። ይህ ከሆነ፣ ቀጣይና ወሳኝ የሆነው ጉዳይ ምን መደረግ አለበት ለሚለው የምንሠጠው ምላሽ ነው። በመሆኑም፣ በመጀመሪያ የአንድነቱ ኃይል ወጥ የሆነ የመፍትኄ ሃሳብ ይዞ መገኘት የሚጠበቅበት ሲሆን ሀገር ለማዳን የሚደረገውን እንቅስቃሴ ትክክለኛ አቅጣጫ በማስያዝ አመራር መስጠት፣ መቀራረብና መደራጀት ከተቀዳሚ ሥራዎቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። የአንድነት ኃይሉን አሁን ካለበት ድክመት ካለበት ድክመት በአፋጣኝ እንዲወጣ ማድረግ ከሁኔታው አስገዳኝነት አንጻር ወሳኝ ነው። በዚህ ደረጃ በተለይ ምሁራን አገራቸው ከነሱ ብዙ ትጠብቃለችና፣ ወደኋላ መለስ ብለው ያለፈውን መንገዳቸውን መመርመና አገራችን ባሁኑ ሰዓት ቅድሚያ የምትሰጠው ለርዕዮተ ዓለም ወይም ለቡድን የፖለቲካ ሥልጣን ሳይሆን ለህልውናዋ መሆኑን በመረዳት ብዕራቸውን ለቀቢፀ ተስፋ ሳይሆን ይህችን ታሪካዊ አገር ለማዳን ቢያነሱና በጋዜጠኛ መሳይ የአገዛዙ ካድሬዎች ጫጫታ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ቅንጥብጣቢ እውቀትና በዘረኞች ወከባ የተወናበደውንና በቀውስ ተዋክቦ መንገዱ የጠፋውን ወገናቸውን አቅጣጫ ቢያሳዩት፣ ታግሎ አገሩን ከጠላት እጅ ማላቀቅ አያቅተውም። አገራችን አሁን ካለችበት ዘርፈ ብዙ ችግርና እያንገበበባት ካለው የህልውና አደጋ ልትወጣ የምትችለው ሉአላዊነቷ ሲከበርና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የተገነባ የሕዝብ አንድነት እውን ሲሆን ብቻ ነው። ዘመናትን ያሰቆጠሩ ያስተሳሰሩና አንድ

ያረጉ እሴቶች ያሉትና በአንድነት በመኖር ረጅም ታሪክ ያላቸው በመሆኑ ተብትበው የያዙትን ችግሮች ምንጭ ነቅሶ በማውጣት፣ በግልፅ ተወያይተውና ተደራድረው መፍትኄዎቹን በጋራ የሕግና አብሮ የመኖር ሥርዓት ለመቅረፅ ሲችሉ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ከአምባገነን ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር የሽግግር ሂደት ዕውን መሆን ይኖርበታል የምንለው። ይህን ስንል ሽግግሩ አልጋ ባልጋ ይሆናል እያልን አይደለም። ብዙ ውጣ ውረዶችና ፈተናዎችም ይገጥሙታል፣ ሆኖም ግን ወደ አውነተኛ ዴሞክራሲ፣ የጠነከረ አንድነት፣ ሰላምና መረጋጋት የሚወስደው መንገድ ይኸው ብቻ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያን ለማዳን የተባበረ ክንዳችን ይጠንክር !!!